# ምዕራፍ አራት

## ወረዳችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የትምህርት ቤቶቻችሁን፣ የመኖሪያ ቤቶቻችሁንና የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ታመለክታላችሁ::
- የአየር፣ የውሃና የአፈር ባህርያትን ትገልጻላችሁ፣ ጥቅማቸውንም ትናገራላችሁ::
- አፈር (ጭቃ) በመጠቀም የተለያዩ መሳይ ቅርጾችንና ምስሎችን ትሰራላችሁ::
- ተክሎችን በመጠናቸውና በዓይነታቸው በመመደብ ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ፣ ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር ታሳያላችሁ::
- እንስሳትን የቤትና የዱር እንስሳት ብላችሁ በመመደብ ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ:: ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር ታሳያላችሁ::
- የተለያዩ የሥራ ዓይነቶችን የግልና የመንግሥት ብላችሁ በመመደብ የሥራን ጥቅም ትናገራላችሁ፣ በዕድሜያችሁ ደረጃ ለሥራ ያላችሁን ክብርና ፍቅር በተግባር ታሳያላችሁ::
- የመጓጓዣን ጥቅም በመናገር የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎች ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ::
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም:- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ ተባብሮ መሥራትንና መመደብን በተግባር ታሳያላችሁ::

## 4.1 የወረዳችን መገኛ

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- <br>• አቅጣጫዎችን ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ በማለት ትለያላችሁ:: <br>• የትምህርት ቤቶቻችሁን፣ የመኖሪያ ቤቶቻችሁንና የጐረቤቶቻችሁን አካባቢያዊ መገኛ ታመለክታላችሁ:: |

**ቁልፍ ቃላት**

- አቅጣጫ
- መገኛ

### 4.1.1 አቅጣጫዎችን መናገር

ተማሪዎች! አቅጣጫ ምንድን ነው? እንዴት ይገለጻል? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ::

አቅጣጫ አንድ ቦታ ወይም አንድ ነገር በአካባቢው ካሉት ቋሚ ነገሮች ለምሳሌ ሕንፃዎች፣ ተራራዎች፣ ወንዞች፣ መንገዶችና ሌሎች ነገሮች አንጻር የሚገኝበት ሥፍራ አመላካች ነው::

የአንድ ቦታ ወይም ነገር አቅጣጫ ለመግለጽ፡-

- ግራና ቀኝ
- አጠገብ
- ፊት ለፊት
- ጀርባ
- ጐን
- ፊትና ኋላ የሚሉትን አቅጣጫ አመላካች ስያሜዎችና ቅጽሎች መጠቀም ይቻላል::

## ከዚህ በታች የሚገኙትን ሥዕሎች አስተውሳችሁ ተመልከቱ

ሀ. በሥዕሉ የሚታዩት ሰው ከዛፉ በየትኛው አቅጣጫ ቆመዋል?



ዛፉ ከሰውየው በስተቀኝ በኩል ወይም አጠገብ ይገኛል

ለ. በሥዕሉ የሚታየው ኳስ ከልጁ በየት በኩል ይገኛል?



ኳሱ በልጁ ግራ እግር አጠገብ ይገኛል

ሐ. በሥዕሉ የሚታየው ሰንደቅ ዓላማ የት ይገኛል?




ሰንደቅ ዓላማው ከመማሪያ ክፍሎቹ ፊት ለፊት ተሰቅሏል

መ. በሥዕሉ ከሚታየው ቤት ጀርባ የሚታየው ምንድን ነው?



ከቤቱ ጀርባ ትላልቅ ዛፎች ይታያሉ

ሠ. በሥዕሉ የሚታዩትን ልጆች መገኛ ተናገሩ::




ዐቢይ ከሃና ፊት ቆሟል ሐና ደግሞ ከዐቢይ ኋላ ቆማለች

ረ. በሥዕሉ ከሚታየው ልጅ በስተቀኝ በኩል የሚገኘው ምንድን ነው? በስተግራ በኩል ያለውስ ምንድን ነው?



ከልጁ በስተግራ የመኖሪያ ቤት፣ በስተቀኝ በኩል ደግሞ ዛፍ ይገኛል::

ሥዕል 4.1 አንጻራዊ መገኛ

## መልመጃ 4.1

**ሀ. የሚከተለውን ሥዕል በመመልከት የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።**




1. *ቤተ መጻሕፍቱ የት ይገኛል?*
2. *የጥበቃ ሠራተኞች ቤት መገኛ የት ነው?*
3. *የመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚገኘው የት ነው?*
4. *የሰንደቅ ዓላማው መገኛ የት ነው?*
5. *ከኳስ መጫወቻ ሜዳው በስተግራ የሚገኘው ምንድን ነው?*
6. *የኳስ መጫወቻውን ሜዳ መገኛ ከሰንደቅ ዓላማው፣ ከመማሪያ ክፍሎችና ከቤተ መጻሕፍቱ አንጻር ግለጹ።*

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከትምህርት ቤታችሁ አንጻር መልሱ።**

1. *የመማሪያ ክፍላችሁ የት ይገኛል?*
2. *የሦስተኛ "ሀ" ተማሪዎች የሚማሩበት ክፍል የሚገኘው የት ነው?*
3. *የተማሪዎች የመጸዳጃ ቤት የት ይገኛል?*
4. *የውኃ ቧንቧው የሚገኘው የት ነው?*
5. *ቤተ መጻሕፍቱ የት ይገኛል?*
6. *የኳስ መጫወቻ ሥፍራው የት ነው?*

## 4.2 በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• የአየርን መኖር በተግባር ታሳያላችሁ።<br>• አየር ለምን እንደሚያስፈልግ ትገልጻላችሁ።<br>• ውኃ በኩሬ፣ በጉድጓድ፣ በምንጮችና በወንዞች እንደሚገኝ ታስረዳላችሁ።<br>• የውኃን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ።<br>• አፈር ለተክሎች የሚሰጠውን ጥቅም ትናገራላችሁ።<br>• በሸክላ አፈር ቀላል መሳይ ቅርጾችንና ምሥሎችን ትሠራላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- አየር
- አፈር
- ውኃ

### 4.2.1 አየር

#### ሀ. አየር ስለመኖሩ

ተማሪዎች! አየር መኖሩን እንዴት እናውቃለን? የአየር መኖርን ለማስረዳት የሚችሉ ምሳሌዎችን መስጠት ትችላላችሁ? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ።

**ቀጥሎ ያሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱ።**



የፊኛ በአየር መሞላት

ሀ. በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



የውሃ ፍልቅልቅታ

ለ. ልጁ ምን እያደረገ ነው?

ሥዕል 4.2 አየር ስለመኖሩ

- *ተማሪዎች! በሥዕሎቹ ከተከናወኑት ተግባራት ምን ተረዳችሁ? እናንተም ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ተመሳሳይ ሙከራዎችን ተግባራዊ አድርጉ::*
- *በተጨማሪም በአየር የተሞላን ፊኛ ወደ ላይ ልቀቁ:: ፊኛው ምን ሆነ? ለምን እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ::*

## ለ. የአየር ጥቅም

*ተማሪዎች! አየር ለምን ለምን ይጠቅማል?*
*ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ::*

**ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ::**


በመተንፈስ ላይ ያለ ልጅ


በአየር የተሞሉ ፊኛዎች


የመኪና ጐማ አየር ሲሞላ

**ሥዕል 4.3 የአየር ጠቀሜታ**

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ለመኖር አየር ያስፈልጋቸዋል:: በተጨማሪም አየር የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ይጠቅማል:: እንስሳትና ተክሎች ለመተንፈስ አየር ያስፈልጋቸዋል::

## መልመጃ 4.2

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. የሰው ልጆች ያለ አየር መኖር ይችላሉ::
2. የመኪና ጐማ ለመሄድ አየር መሞላት አለበት::
3. ዕፅዋት አየር አያስፈልጋቸውም::

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ሰዎች የሚተነፍሱት ነገር ምንድን ነው?
2. ተክሎች አየር ባያገኙ ምን ይሆናሉ?

## 4.2.2. ውኃ

### ሀ. የውኃ መገኛ

***ተማሪዎች! ውኃ የት የት ይገኛል? ከጓደኞቻችሁ ጋር እየተወያያችሁ በዝርዝር ጻፉ፡፡***
በአካባቢያችሁ ውኃ ከየት ከየት እንደሚገኝ ጥቀሱ፡፡

**የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ**



የቧንቧ ውኃ



የጉድጓድ ውኃ



የሐይቅ ውኃ



የምንጭ ውኃ



የወንዝ ውኃ



የዝናብ ውኃ

ሥዕል 4.4 የውኃ መገኛ

ተማሪዎች! ውኃ ከምን ከምን እንደሚገኝ ከሥዕሎቹ ተገነዘባችሁ?

የውኃ መገኛዎች ብዙ ናቸው።

**ውኃ**

- ከቧንቧ
- ከጉድጓድ
- ከኩሬ
- ከሐይቅ
- ከምንጭ
- ከውቅያኖስ
- ከወንዝ
- ከባሕር
- ከዝናብ ይገኛል።

## ሀ. የውኃ ጥቅም

ውኃ ለምን ለምን ይጠቅማል? ያለ ውሃ መኖር እንችላለን? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ተመልከቱ።



ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ሴትየዋ ምን እየሠራች ነው?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምን እያደረገ ነው?




ከሥዕሉ ምን ትረዳላችሁ?



ሥዕሉ ምን ያሳያል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

ሥዕል 4.5 የውኃ ጥቅም

ውኃ ለሰዎችና ለእንስሳት በመጠጥነት ያገለግላል። ተክሎችም ለዕድገታቸውና ምግባቸውን ለማዘጋጀት ውኃ ይፈልጋሉ። በተጨማሪም ውኃ ለግል ንጽሕና መጠበቂያ፣ ለልብስና ለዕቃ ማጠቢያ እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ይጠቅማል።

## መልመጃ 4.3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. እናንተ የምትጠጡት ውኃ የሚገኘው ከየት ነው?
2. የወንዝ ውኃ ቢጠጣ ምን ችግር ያስከትላል?
3. የውኃ መገኛ ከሆኑት ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ።

## አፈር

ተማሪዎች! አፈር ለምን ለምን ይጠቅማል? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ::

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ጥያቄዎቹን መልሱ::



ዛፉ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ያስቻለው ምንድ ነው?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?

ሥዕል 4.6 የአፈር ጥቅም

ከዚህ በታች የሚታዩት ሥዕሎች ምን ምን ናቸው? ከምን ከምን የተሠሩ ይመስላችኋል?



ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል?



ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድነው?

ሥዕል 4.7 ከአፈር የሚሠሩ መገልገያ ዕቃዎች

**ተማሪዎች!**

**አፈር፡-**

- ለእርሻ ሥራ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡
- ተክሎች እንዳይወድቁና ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ይረዳል፡፡
- ተክሎች በሥሮቻቸው አማካኝነት ውኃ እንዲስቡ ያስችላቸዋል፡፡
- የቡና ጀበና፣ የሸክላ ድስትና የእንጀራ ምጣድ እንዲሁም መሳይ ቅርጾችን ለመሥራት ያገለግላል፡፡

## መልመጃ 4.4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. አፈር ለምን ይጠቅማል?
   ሀ. ቤት ለመሥራት
   ለ. ተክሎች ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ለመርዳት
   ሐ. ተክሎች በሥሮቻቸው አማካኝነት ውኃ እንዲስቡ ለመርዳት
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው
2. ከሚከተሉት ውስጥ ከአፈር የማይሠራው የቱ ነው?
   ሀ. የቡና ጀበና ሐ. መኪና
   ለ. ማሰሮ መ. የእንጀራ ምጣድ

**ተግባራዊ ሥራ**

ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ሸክላ አፈር በመፈለግ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 4.3. በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• ተክሎችን በመጠናቸው ለይታችሁ ትመድባላችሁ፡፡<br>• የተክሎችን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ፡፡<br>• ስለተክሎች እንክብካቤ ትናገራላችሁ፡፡<br>• የቤትና የዱር እንስሳትን ትለያላችሁ፡፡<br>• የእንስሳትን ጥቅሞች ትናገራላችሁ<br>• ስለ እንስሳት እንክብካቤ ትገልጻላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- ሕይወት ያላቸው ነገሮች
- ተክሎች
- የቤት እንስሳት
- የዱር እንስሳት

## 4.3.1 ተክሎች

ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ምን ምን የተክል ዓይነቶች ይገኛሉ?

በአካባቢያችሁ የሚገኙ ተክሎች ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

ከመምህራችሁ ጋር በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ የሚገኙትን ተክሎች ተመልከቱ:: በጉብኝታችሁ ወቅት የምትመለከቷቸውን ተክሎች ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ ተክሎች በማለት መድቧቸው:: ከዚያም ወደ ክፍላችሁ በመመለስ ውይይት አድርጉ::

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ስማቸውንና ለምን እንደሚጠቅሙ ግለጹ::



በሥዕሉ የሚታየው ተክል ምንድነው? ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



ይህ ተክል ምን ይባላል? የሚሰጠው ጥቅም ምንድ ነው?



ይህ ሥዕል የሚያሳየው ምንን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ተክል ምንድን ነው? ለምን ይጠቅማል?



ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



ይህ ሥዕል የሚያሳየው ምንን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?

ሥዕል 4.8 የተክል ዓይነቶችና ጠቀሜታቸው

## ተክሎችን መመደብ

**ተማሪዎች! የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ በመገልበጥ በመጽሐፋችሁ በሥዕል 4.8 የሚታዩትን የተክል ዓይነቶች ዛፍ፣ ቁጥቋጦና ትንሽ ተክል በማለት መድቡ።**

**በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የሚከተለውን «✓» ምልክት አስቀምጡ።**

| | የተክሉ ስም | የተክሉ ምድብ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዛፍ | ቁጥቋጦ | ትንሽ ተክል |
| 1 | ዘንባባ | ✓ | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | ቲማቲም | | | ✓ |
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |

ተክሎች የተለያየ ጠቀሜታ አላቸው:: ለምሳሌ:-

- ለምግብነት
- ለጌጣጌጥ መሥሪያነት
- ለውበትነት
- ለአጥር
- ለቤት ግንባታ
- ለማገዶነትና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ::

## ለተክሎች የሚደረግ እንክብካቤ

ተማሪዎች! ተክሎችን መንከባከብ ለምን ያስፈልጋል? እናንተ በመኖሪያ ቤታችሁና በትምህርት ቤታችሁ ለሚገኙ ተክሎች ምን ምን እንክብካቤ ታደርጋላችሁ?

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለተክሎች የሚደረግላቸውን እንክብካቤና ጠቀሜታ ለንደኛችሁ ግለጹ::



በሥዕሉ የሚታዩት ልጆች ምን እያደረጉ ነው? የሚያደርጉት እንክብካቤ ለምን ይጠቅማል?



ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ? ይህ ተግባር ምን ያስከትላል?



ልጆቹ ምን እየሠሩ ነው? ይህ ተግባር ለምን ይጠቅማል?

ሥዕል 4.9 ለተክሎች የሚደረግ እንክብካቤ

**ተማሪዎች!** ለተክሎች የሚደረጉ እንክብካቤዎችንና ጠቀሜታቸውን ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ተመልከቱ::

**ሠንጠረዥ 4.1 የተክሎች እንክብካቤና ጠቀሜታቸው**

| ተ.ቁ | የእንክብካቤ ዓይነት | እንክብካቤ የሚሰጠው ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| 1 | ውኃ ማጠጣት | ተክሎች እንዳይጠወልጉ ይረዳል:: |
| 2 | አረም ማረም | ተክሎች እንዳይቀጭጩ ይጠቅማል:: |
| 3 | መኮትኮት | በቂ አየር እንዲያገኙ ያግዛል:: |
| 4 | ማደበሪያ መስጠት | ተክሎች እንዲፋፉ ይጠቅማል:: |
| 5 | በእንስሳት እንዳይጎዱ መጠበቅ | ተክሎች እንዳይደርቁ ይረዳል:: |
| 6 | ያለ አግባብ አለመቁረጥ | ተክሎች እንዳይደርቁ ይጠቅማል:: |
| 7 | ንጽሕናቸውን መጠበቅ | ተክሎች እንዳይደርቁና በበሽታ እንዳይጎዱ ይረዳል:: |

## መልመጃ 4.5

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ተክሎች ከሚሰጡት ጥቅም ሦስቱን ግለጹ::
2. በተክሎች ላይ ቆሻሻ ውኃ መድፋት ምን ችግር ያስከትላል?
3. ተክሎችን ለመንከባከብ ምን ምን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል?
4. ቲማቲምና ካሮት ከየትኛው የተክል ዓይነት ይመደባሉ?
5. አረምን ማረም ለምን ይጠቅማል?

## 4.3.2 እንስሳት

### ሀ. የእንስሳት አመዳደብ

ተማሪዎች! ምን ምን ዓይነት እንስሳትን ታውቃላችሁ?

የቤት እንስሳት ምንድን ናቸው?

የዱር እንስሳት ምንድን ናቸው?

**የቤት እንስሳት:-** ከሰዎች ጋር ተጠግተው የሚኖሩ ለማዳ እንስሳት ናቸው፡፡

**የዱር እንስሳት:-** ከሰዎች ርቀው በዱር (በጫካ) ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው፡፡


**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት እንስሳቱን የቤትና የዱር እንስሳት በማለት መድቧቸው፡፡**



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምንድን ነው?
እንስሳው በየትኛው ምድብ ይገኛል?




ሥዕሉ ምንን ያሳያል? የሚገኝበትን ምድብ ግለጹ፡፡



ይህ የምን ሥዕል ነው? በየትኛው ምድብ ይገኛል?




በሥዕሉ የሚታየው ምንድንነው? ምድቡን ግለጹ፡፡



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? በምን ምድብ ውስጥ ይገኛል?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምንድነው? የሚገኝበትን ምድብ ግለጹ



ይህ የምን ሥዕል ነው? ምድቡን ተናገሩ።



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? በየትኛው ምድብ ይገኛል?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምን ይባላል? በየትኛው ምድብ ይገኛል?

ሥዕል 4.10 የቤትና የዱር እንስሳት

ተማሪዎች! በሥዕሉ ላይ የቀረቡት እንስሳት በግ፣ አህያ፣ ድመት፣ ዶሮና ላም የቤት እንስሳት (ለማዳ እንስሳት) ሲሆኑ ነብር፣ ዝንጀሮና አንበሳ ደግሞ የዱር እንስሳት ናቸው።

### ሰ. የእንስሳት ጥቅም

በሚከተለው ሠንጠረዥ የቀረበውን ምሳሌ በማድረግ እያንዳንዱ እንስሳ የሚሰጠውን ጥቅም ጻፉ::

| የእንስሳው ስም | እንስሳው የሚሰጠው ጥቅም |
|---|---|
| ላም | ወተት፣ ሥጋ |
| ዶሮ | |
| በግ | |

### ተግባራዊ ክንውን

በሚከተለው ሠንጠረዥ የቀረበውን ምሳሌ በማድረግ እያንዳንዱን ጥቅም የሚሰጡ እንስሳትን ስም ጻፉ

| የእንስሳው ስም | ከእንስሳው የሚገኘው ጥቅም |
|---|---|
| አህያ | ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቅማል:: |
| | ለእርሻ ሥራ ያገለግላል:: |
| | ጋሪ ይጎትታል:: |
| | ፀጉሩ ለልብስ መሥሪያነት ይጠቅማል:: |
| | ቤትን ከሌባ ይጠብቃል:: |
| | አይጥ የሚያደርሰውን ጥፋት ይከላከላል:: |

የእንስሳት ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው::

- ለምግብነት
- ለመጓጓዣነት
- ለመዝናኛነት
- ለገቢ ምንጭነት
- ለጥበቃ ሥራ
- ለአልባሳትና ለመሳሰሉት በጥሬ ዕቃነት ያገለግላሉ::

## መልመጃ 4.6

ሀ. በ"ሀ" ሥር የቀረቡትን በ"ለ" ሥር ከቀረቡት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቀንድ | ሀ. የብርድ ልብስ ለመሥራት ይጠቅማል |
| 2. ጠፍር | ለ. ለምግብነት ይጠቅማል |
| 3. ቆዳ | ሐ. ለጌጣጌጥ መሥሪያ ይጠቅማል |
| 4. የበግ ፀጉር | መ. ለአልጋ መሥሪያ ያገለግላል |
| 5. የዱር እንስሳ | ሠ. ለገቢ ምንጭነት ይጠቅማል |
| | ረ. ለጫማ መሥሪያ ይጠቅማል |
| | ሰ. ለመድኃኒትነት ያገለግላል |

### ሐ. ለእንስሳት እንክብካቤ ማድረግ

ተማሪዎች! እንስሳትን ለምን እንከባከባለን?
ለእንስሳት የሚደረግ እንክብካቤ መገለጫዎች ምን ምንድን ናቸው?
ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ ግለጹ።

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለእንስሳቱ የሚደረገውን እንክብካቤ ግለጹ።



በሥዕሉ የምትታየው ድመት ምን እያደረገች ነው?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?



እንስሳቱ ምን እያደረጉ ነው?

ሥዕል 4.11 ለእንስሳት የሚደረግ እንክብካቤ

**ተማሪዎች!** እንስሳት ጤናማ እንዲሆኑና ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጡን እንክብካቤ ልናደርግላቸው ይገባል፡፡ እንስሳትን፡-

- በመመገብ
- ውሃ በማጠጣት
- መጠለያቸውን በመጠበቅ
- ንጽሕናቸውን በመጠበቅ
- ባለመምታት
- ባለመተናኮል መንከባከብ ይኖርብናል፡፡

## መልመጃ 4.7

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የእንስሳትን ንጽሕና በመጠበቅ የምንከባከበው ለምንድን ነው?
2. እንሰሳትን መተናኮል ምን ያስከትላል?
3. ለእንስሳት ምግብ በመስጠት የምንከባከበው ለምንድን ነው?

## 4.4 በአካባቢያችን የተለመዱ የሥራ ዓይነቶች

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የሥራን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ፡፡
- የሥራ ዓይነቶችን የግል ሥራ፣ በግለሰብ በመቀጠር የሚሠራ ሥራና የመንግሥት ሥራ በማለት ትመድባላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁና በቤቶቻችሁ የሚከናወኑ ቀላል ሥራዎችን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- *ሥራ*
- *የሥራ ዓይነቶች*

## 4.4.1. የሥራ ጥቅም

*ተማሪዎች! ሥራ መሥራት ለምን ይጠቅማል?*
*በወረዳችሁ ነዋሪዎች በስፋት የተለመዱ የሥራ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?*

ሥራ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ይጠቅማል:: የማይሠሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማግኘትና ሕይወታቸውን መለወጥ አይችሉም:: ስለዚህ ሥራ ራስን ለመቻልና የሌሎች ጥገኛ ላለመሆን የሚከናወን ተግባር ነው::

*ተማሪዎች! ወላጆቻችሁ ሥራ በመሥራት ገቢ ባያገኙ ኖሮ ምን ዓይነት ችግር ይኖር ነበር?*

## 4.4.2. የሥራ ዓይነቶች

*ተማሪዎች! የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::*




- *ሥዕሉ ምንን ያሳያል?*
- *በሥዕሉ የሚታየው ሰው የሚተዳደረው በምንድን ነው?*



- *በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?*
- *በሥዕሉ የሚታየው ሰው እያከናወነ ያለው ስራ ምን በመባል ይታወቃል?*



• በሥዕሉ የምትታየው ሴት የምትሠራው ሥራ ምንድን ነው?



በሥዕሉ የምትታየው ሴት የተሠማራችው በምን ሙያ ነው?



• ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?
• በሥዕሉ የሚታየውና ነጭ ገዋን የለበሰው ሰው በምን ይተዳደራል?



• በሥዕሉ የሚታዩት ሰዎች የሚተዳደሩት በምንድን ነው?

ሥዕል 4.12 የሥራ ዓይነቶች

የሥራ ዓይነቶች በሦስት ይመደባሉ:: እነርሱም:-

- የመንግሥት ሥራ
- የግል ሥራና
- ለግለሰብ ተቀጥሮ መሥራት ናቸው::

## መልመጃ 4.8


**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ የመልሱን ፊደል አክብቡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የመንግሥት ሥራ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. የጉልት ንግድ
   - ሐ. ሽመና
   - ለ. የሸክላ ሥራ
   - መ. ዳኝነት
2. ከሚከተሉት የግል ሥራ የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ፖሊስነት
   - ሐ. ልብስ ስፌት
   - ለ. ዳኝነት
   - መ. የወረዳ አስተዳዳሪነት
3. ከሚከተሉት ውስጥ የሥራ ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. መሠረታዊ ፍላጐት ማሟላት
   - ሐ. የሌሎች ጥገኛ መሆን
   - ለ. ሕይወት መለወጥ
   - መ. ራስን መቻል
4. ከሥራ ዓይነት የማይመደበው የትኛው ተግባር ነው?
   - ሀ. የጉልት ንግድ
   - ሐ. የጉልበት ሥራ
   - ለ. ልመና
   - መ. የጽዳት ሥራ

### 4.4.3 በሥራ መኩራት

ተማሪዎች! ቤተሰቦቻችሁን ምን ምን ሥራዎችን በመሥራት ታግዛላችሁ?
ቤተሰብን በሥራ ማገዝ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ፡፡**



በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?





ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

ሥዕል 4.13 ቤተሰብን በሥራ መርዳት

**ተማሪዎች!** ቤተሰብን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን መርዳት ይኖርብናል፡፡ በቤታችን ውስጥ በአቅማችን የምናከናውነው ሥራ አካላችን እንዲጠነክር፣ ሥራን እንድንለምድና ቤተሰቦቻችንን እንድናግዝ ይረዳናል፡፡ ስለዚህም በቤታችን ውስጥ በምንሠራው ሥራ ኩራት ሊሰማን ይገባል፡፡

## መልመጃ 4.9

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. በግብርና ሙያ የተሰማሩ ሰዎች ሥራቸውን በደንብ ባይሠሩ ምን ሊከሰት ይችላል?
2. የመኪና አሽከርካሪ መኪናውን በአግባቡ ባያሽከረክር ምን ሊፈጠር ይችላል?
3. በዳቦ ቤት ዳቦ የሚጋግሩ ሰዎች ዳቦውን በንጽሕና ባይጋግሩ ምን ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል?
4. ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ባይማሩ ምን ችግር ይፈጠራል?

## 4.5 የአካባቢያችን መጓጓዣ

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
|---|
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• የመጓጓዣን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ፡፡<br>• የባህላዊ የመጓጓዣ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡<br>• የዘመናዊ መጓጓዣ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- ባህላዊ መጓጓዣ
- ዘመናዊ መጓጓዣ

## 4.5.1 የመጓጓዣ ጥቅም

ተማሪዎች! መጓጓዣ ምንድን ነው? ምንስ ጥቅም ይሰጣል? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ::

መጓጓዣ ሰውን ወይም ዕቃን ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት ነገር ነው::
የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለት ናቸው:: እነርሱም:-

1. ባህላዊ መጓጓዣና
2. ዘመናዊ መጓጓዣ ናቸው::

### 1. ባህላዊ መጓጓዣ

ተማሪዎች! የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ በመመልከት ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ::



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ይህ እንስሳ ለምን ይጠቅማል?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ይህ እንቅስቃሴ በስፋት የሚታየው በየት አካባቢ ነው?



በሥዕሉ የሚታው እንስሳ በየት አካባቢ ይገኛል? ለምንስ ይጠቅማል?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ለምንስ ያገለግላል?

ሥዕል 4.14 ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

## 2. ዘመናዊ መጓጓዣ

**ተማሪዎች! ዘመናዊ መጓጓዣ ማለት ምን ማለት ነው? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ::**

**ተማሪዎች! ሥዕሉን በመመልከት የጥያቄዎቹን መልሶች ለመምህራችሁ ንገሩ::**



በሥዕሉ የሚታየው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል? ለምንስ ይጠቅማል?



ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው? ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ጥቅም ይሰጣል?




ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ከሌሎቹ የሚለየው በምንድን ነው?



ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል? ከሌሎቹ በምን ይለያል?

**ሥዕል 4.15 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች**

**ተማሪዎች!** አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ግመልና ጋሪ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ናቸው:: ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የመኪና መንገድ በሌለባቸው አካባቢዎች ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማሉ:: ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት መኪናን፣ ባቡርን፣ አውሮፕላንን፣ መርከብንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ፈጣን ናቸው::

## መልመጃ 4.10

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የመጓጓዣ ዓይነቶች በስንት ይመደባሉ? ስማቸውን ጥቀሱ።
2. አህያ በየትኛው የመጓጓዣ ዓይነት ውስጥ ይመደባል?
3. መጓጓዣ ለምን ለምን ይጠቅማል?
4. ፈጣን ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት ማለት ምን ማለት ነው?
5. የመኪና መንገድ በሌለበት አካባቢ ሰዎችን ለማጓጓዝ የሚያገለግለው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል?
6. ብዙ ሰዎችንና ዕቃዎች በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ የሚያስችለው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል?

## ማጠቃለያ

- አቅጣጫ አንድን ቦታ ለመጠቆም ወይም ለማመልከት የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ግራ፣ ቀኝ፣ ከፊት፣ ከኋላ፣ አጠገብ፣ መካከል የሚሉትን ስያሜዎች በመጠቀም የአንድን ነገር መገኛ ማመልከት ይቻላል፡፡
- በአካባቢያችን የተለያዩ ሕይወት የሌላቸው ጠቃሚ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ አየር፣ አፈርና ውኃ በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ አፈር ለተክሎች ዕድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ውኃ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ሕልውና እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ውኃ ለመጠጥነት፣ ለማጠቢያ፣ ለተክሎች፣ ለምግብ ማብሰያነት ይጠቅማል፡፡ ውኃ ከዝናብ፣ ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከቧንቧና ከመሳሰሉት ሊገኝ ይችላል፡፡
- እንስሳትና ዕፅዋት በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ዕፅዋት (ተክሎች) በመጠናቸው ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ ተክሎች ተብለው ይመደባሉ፡፡ እንስሳት ደግሞ የዱር እንስሳት እና የቤት እንስሳት ተብለው ይመደባሉ፡፡ የዱር እንስሳት ከሰው ርቀው በየዱሩና በየበረሃው ይኖራሉ፡፡ የቤት እንስሳት ደግሞ ከሰው ተጠግተውና ተላምደው ይኖራሉ፡፡ እንስሳትና ዕፅዋት ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው፡፡
- በአካባቢያችን በስፋት የተለመዱ ልዩ ልዩ የሥራ ዓይነቶች አሉ፡፡ የሥራ ዓይነቶች የመንግሥት ሥራ፣ የግል ሥራ እና ለግለሰብ ተቀጥሮ መሥራት ተብለው ይመደባሉ፡፡ ሥራ ምግብን፣ ልብስንና መጠለያን ለማግኘት ይጠቅማል፡፡
- መጓጓዣ ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማል፡፡ የመጓጓዣ ዓይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የመኪና መንገድ በሌለባቸው አካባቢዎች ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማሉ፡፡ ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ደግሞ ብዙ ሰዎችንና በርካታ ዕቃዎችን በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ ይረዳሉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ልጆች ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት የለባቸውም::
2. አየር፣ አፈር እና ውኃ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው::
3. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ፈጣንና ርካሽ ናቸው::
4. ውሻ የዱር እንስሳ ነው::
5. ሥራ መሥራት ምንም ጥቅም የለውም::

**ለ. በ"ሀ" ሥር የተቀመጡትን በ"ለ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ግራና ቀኝ | ሀ. ለመተንፈስ ይጠቅማል |
| 2. አየር | ለ. የዱር እንስሳ |
| 3. ዶሮ | ሐ. የዱር እንስሳት መኖሪያ |
| 4. ነብር | መ. የቤት እንስሳት መኖሪያ |
| 5. ደን | ሠ. አቅጣጫዎች |
| | ረ. የቤት እንስሳ |
| | ሰ. ባህላዊ መጓጓዣ |
| | ሸ. ዘመናዊ መጓጓዣ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ሕይወት ያለው ነገር የትኛው ነው?
   ሀ. ውኃ ለ. ተክል ሐ. አፈር መ. አየር
2. የውኃ ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ለመጠጥ ሐ. ለንፅህና
   ለ. ለተክሎች እድገት መ. ሁሉም መልስ ናቸው
3. ተክሎች ለምን ጥቅም ይውላሉ?
   ሀ. ለምግብነት ሐ. ለአካባቢ ውበት
   ለ. ለማገዶ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
4. ከሚከተሉት ውስጥ የዱር እንስሳ የሆነውን ለዩ::
   ሀ. ነብር ለ. ድመት ሐ. በግ መ. አህያ
5. እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንችላለን?
   ሀ. በመመገብ ሐ. ባለመተናኮል
   ለ. መጠለያ በማዘጋጀት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ፡፡*

1. የትምህርት ቤቱን፣ የመኖሪያ ቤቱንና የወረዳዬን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት እችላለሁ፡፡ ☐
2. የአየር፣ የውሃና የአፈር ባሕርያትን እገልጻለሁ፣ ጥቅማቸውን አስረዳለሁ፡፡ ☐
3. አፈር (ጭቃ) በመጠቀም የተለያዩ መሳይ ቅርጾችንና ምስሎችን እሠራለሁ፡፡ ☐
4. ተክሎችን በመጠናቸውና በዓይነታቸው በመመደብ ጥቅማቸውን እናገራለሁ፤ ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
5. እንስሳትን የቤትና የዱር እንስሳት በማለት በመመደብ ጥቅማቸውን እናገራለሁ፡፡ ለእንስሳት የሚደረገውን እንክብካቤ እገልጻለሁ፡፡ ☐
6. የተለያዩ የሥራ ዓይነቶችን የግል ሥራና የመንግሥት ሥራ ብዬ በመመደብ የሥራ ጥቅምን እናገራለሁ፡፡ ☐
7. ለሥራ ያለኝን ክብርና ፍቅር በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐
8. የመጓጓዣን ጥቅም በመናገር የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ ምሳሌዎች እሰጣለሁ፡፡ ☐
9. ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ ተባብሮ መሥራትንና መመደብን በተግባር አሳያለሁ፡፡ ☐